የሰ/መ/ቁ 42706

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር -ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሳሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጥበቃ ሰራተኛነት በአመልካች ድርጅት ሳገለግል ቆይቼ ምንም ሳላጠፋ ከሥራ አሰናብቶኛል ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ይህ ካለሆነ የአንድ ወር ደሞዝና ሌሎች የስንብት ክፍያ ይከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በሰጠው መልስ ተጠሪ መጠጥ ጠጥተው ወደ ሥራ በመግባት አምቧጋሮ ይፈጥራሉ፣ ከባልደረባቸው አይግባቡም በዚህም መሠረት የማስጠንቀቅያ ጽሑፍ ቢሰጣቸውም ሊታረሙ ባለመቻላቸው የ10 ቀን ደሞዝ ተቀጥተዋል ስለዚህ ስንብታቸው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም አመልካች ተጠሪን ለማሰናበት ምክንያት ናቸው ሲል የገለፀው ወይም ያቀረበው ማስረጃ እርስ በርሱ የሚቃረን ነው በተለይም በ8/7/2000 እና በ11/8/2000 ለተጠሪ የተፃፉት ማስጠንቀቂያ የሚጣረስ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በመሆኑም የተጠሪ የ1 (አንድ) ወር ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ክፍያን አስመልክቶ በተጠሪ ጥያቄ መሠረት እንዲከፈለው ሲል ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄን አልተቀበልኩም ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቧል፡፡ መዝገቡ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 13/2001 ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሠረት የሰበር ችሎትም ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነውም አመልካች ክሱን ለማስተባበል ያቀረባቸው ምስክሮች ሣይሰሙ ውሳኔ የመሠጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሥራ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ አመልካች ያለ ጥፋት አሰናበተኝ ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ካልሆነም በሕግ የተቀመጠውን ይክፈለኝ ሲሉ በጠየቁት መሠረት አመልካችም ተጠሪ ጥፋት በመፈፀማቸው ነው ያሰናበትኳቸው ሲል ተከራክሮ፤ ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪ የፈፀሙትን ጥፋት አላስረዳም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል ወደሥራ የመመለስ ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የተለያዩ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈለው ውሣኔ ሰጥቷል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ውሣኔውን ጉድለት የለበትም በማለት አፅንቷል፡፡

እኛም ከላይ የተጠቀሰውን የውሣኔ አሰጣጥ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምተናል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አመልካች ያቀረበው ማስረጃ በተለያዩ ጊዜ ለተጠሪ የተፃፈ ማስጠንቀቂያ የስንብቱን ምክንያት በአግባቡ የማያረጋግጥና የተጣረሰ (የሚጋጭ) ነው በማለት ነው፡፡ ስለ አመልካች የሰው ማስረጃም ቢሆን በውሣኔው ላይ የጠቀሰው ነገር የሌለ እና መስማት የማያስፈልገው እንኳ ቢሆን የገለፀው ነጥብ የለም አመልካች በመከላከያው መልስ የሰው ምስክር እስከቆጠረ ድረስና የቀረበው የሠነድ ፅሁፍ በአግባቡ የተጠሪን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥለት ከሆነ አግባብነት ያለው ውሣኔ ለመስጠት ሲባል የአመልካችን ምስክር መስማትና ወደ ውሣኔ ሊመጣ ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም የአመልካች የቀረበበትን ክስ የመከላከል መብቱ ሊታለፍ የማይገባው ህጋዊ ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው ምስክር ሣይሰማ ወደ ውሣኔ መድረሱ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት ሣያርመው ማለፉ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13385 በቀን 15/9/2001 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 75596 በቀን 12/5/2001 የተሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የሰው ምስክር በመስማት ይወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14227 ላይ ተላልፎ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተው ይጻፍ፡፡
4. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ